# ሰርድሚል ተቋም
## የወንጌል ስርጭት ባጅ

*ኢየሱስም ቀርቦ እንዲህ አላቸው፡- "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።*

ማቴዎስ 28፡18-20

እነዚህ በማቴዎስ ወንጌል የሚገኙ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከመወሰዱ በፊት የተናገራቸው የመጨረሻ ቃላት ናቸው። እናንተም የመጨረሻ ቃሎቻችሁን የማካፈል እድል ካገኛችሁ ቅርባችሁ ለሆኑ ሰዎች ምን ልትሉ እንደምትችሉ አስቡ። ምን ቃላት ትናገሩ ይሆን? እነዚያ ቃላት ስለ አየር ሁኔታ፣ ስለ ስራችሁ ወይም ስለ እናንተ ስለምትወዱት የስፖርት ቡድን የቅርብ ጊዜ የፍጻሜ ነጥባቸው አይሆኑም። ለልብዎ በጣም ቅርብ የሆኑ ነገሮች ይሆናሉ እንጂ። ለኢየሱስም እንደዚሁ ነበር። እንዲሰሙት በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነገር አካፈላቸው። ደቀ መዛሙርት ማፍራት በልቡ የከበደ ሃሳብ ነበር። የኢየሱስ ተልዕኮና ትልቁ ናፍቆት የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ማስፋፋትና ደቀ መዛሙርትን (ተከታዮችን) ማፍራት ነው። ደቀ መዛሙርት የማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ ወንጌል መስበክ ነው። በዚህ ባጅ ውስጥ ወንጌልን ባሉበት አውድ ውስጥ ማካፈል ምን ማለት እንደሆነ እና እንዴት ማድረግ እንዳለብዎ ይወያያሉ። በተጨማሪም፣ ጌታን ከማያውቅ ሰው ጋር ምስክርነትዎን ለማካፈል እድል ይኖርዎታል።

## ባጁ የሚያካትተው፡-

**የወንጌል አቀራረብ** - በወንጌል አቀራረብ ውስጥ ምን መካተት እንዳለባቸው ትመለከታላችሁ
**የግል ምስክርነት** - ወንጌልን ለማካፈል የራስዎን ምስክርነት እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ይወያያሉ።
**የወንጌል ስርጭት ልምድ** - ያዳበርከውን ችሎታ ለአንድ ሰው ለማካፈል ትጠቀማለህ

## የውይይት ርዕሶች፡-

1. ይህንን ጥያቄ በራስዎ ቃላት ይመልሱ፡- ወንጌል ምንድን ነው? መልሱን በቡድናችሁ ተወያዩ።
2. የወንጌል ሥርጭት አገልግሎት በአገርህ ምን ይመስላል? እንዴትስ ይታያል? በእርስዎ ክልል ውስጥ የተለመደ የወንጌል ስርጭት መንገድ ምንድን ነው?
3. በወንጌል አቀራረብ ውስጥ መካተት ያለባቸው ዋና ዋና ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ዝርዝር ያዘጋጁ። ከዚያም ያንን ዝርዝር ወደ 6 ንጥብ ወይም ከዚያ በታች ለማሳነስ ይሞክሩ።
4. በአገርዎ ወንጌልን ለማካፈል በጣም ውጤታማው መንገድ የትኛው ነው? ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር ማካፈል ነው ወይስ አስቀድመው ግንኙነት ከነበሯቸው ሰዎች ጋር ማካፈል ነው?
5. ከምታውቀው ሰው ጋር እና ከማታውቀው ሰው ጋር እንዴት ወንጌልን ታካፍላለህ?
6. በአገራችሁ ወንጌል ማካፈል አደጋ አለው? ይህ ለሌሎች ወንጌልን በምታካፍልበት ጊዜ ምን አይነት ተጽዕኖ ያሳድርቦታል?

## የግል ምስክርነት፡-

ሁሉም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ወደ ማመን እንዴት እንደ መጡ የራሳቸው የሆነ ታሪክ ወይም የግል ምስክርነት አላቸው። ምስክርነትህ በሌላ ሰው ህይወት ውስጥ ለውጥ ለማምጣት በማንኛውም ጊዜ ልትጠቀመው የምትችል ጠንካራ ምስክር ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ የተቀበልክበት ጊዜ እንዴት እንደነበር አስብ። ከሰዎች ጋር ልታካፍለው የምትችለውን የ3 ደቂቃ ያህል አጭር ምስክርነት ታዘጋጃለህ።

ምስክርነትዎን በምታዘጋጅበት ጊዜ ሊያስቡባቸው የሚገቡ ሶስት ጠቃሚ ምክሮች እንሰጣችሁ።

<u>አንደኛ</u>፡- ኢየሱስን ከማወቃችሁ በፊት ህይወታችሁ ምን ይመስል ነበር? ይህ ከምታነጋግሩት ሰው ጋር እንዴት ሊገናኝ ይችላል?

<u>ሁለተኛ</u>፡- ስለ ኢየሱስ ያወቅህበትና በእርሱ ላይ እምነት የጣልክበት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ወንጌል እውነት መሆኑን እንድታዩ ያደረገህ ምንድን ነው?

<u>ሦስተኛ</u>፡-ሌላ ሰው ከራሱ ጋር ሊያዛምደው የሚችል በክርስቶስ ላይ እምነትህን ካደረክ በኋላ በሕይወትህ ውስጥ ምን ተለወጠ?

## የትግበራ ጥሪ፡-

1. ምስክርነትዎን ይፃፉ፣ በቃል ይያዙትና ከአሰልጣኝዎ እና ከሌሎች በቡድንዎ ውስጥ ካሉት ጋር ያካፍሉ።
2. ምስክርነትህን ክርስቲያን ላልሆነ ሰው አካፍል።
3. እንዴት እንደሆኑ ከአሰልጣኝዎ እና ከቡድንዎ ጋር ተወያዩ። ጥሩ ያለፈው ምን ነበር? ምን ማሻሻል ይችላሉ?

## የባጅ መስፈርት፡-

ይህ ባጅ የመሠረታዊ ትምህርቶች አንደኛው ክፍል ሲሆን ተማሪው ***ወደ ተግባራዊነት*** የሚለውን የትምህርት ክፍል ከ ***ባጁ የሚያካትተው*** እና ***ለውይይት ከቀረቡት ርዕሶች*** አንጻር በታማኝነት እና ባለማቋረጥ በተሳካ ሁኔታ ኮርሱን በሙሉ ሲያጠናቅቅ በሰርድ ሚል ኢንስቲቱት ይሸለማል።